# የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

Purpose Black ETHIOPIA

2015 ሰኔ ቅጽ 1 ቁጥር 16


## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የታወር ሼር ሆልደር ሞዴል ባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጉባኤ አካሄደ።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሰኔ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ቀደም ሲል ከግንቦት 21-ሰኔ 6 በማስታወቂያ ዋጋ የተከናወነውን ባለ 3 መኝታ ቤት በስጦታነት በሚያስገኘውና የ1.5 ሚሊዮን ብር ተመን ባለው አክሲዮን ሽያጭ የተሰበሰበውን 1 ቢሊዮን ብር ሕገወጥ እግድ በተመለከተ የታወር ሼር ሆልደር ሞዴል ባለአክሲዮኖችን የመጀመሪያ አስቸኳይ ጉባኤ በኩባንያው መሰብሰቢያ አዳራሽ አካሔደ።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በዓይነቱ ልዩ እና ግዙፍ የሆነውን የከገበሬው ሕንጻ ለመገንባት እንቅስቃሴ መጀመሩን ተከትሎ እስከአሁን ከነበሩት መደበኛና ፍራንቻይዝ አክሲዮኖች በተጨማሪነት ያስተዋወቀው ይህ የታወር ባለአክሲዮን ሥርዓት በመጀመሪያው ዙር በ100 ካሬ ሜትር መሬት ላይ የሚያርፍ ባለ 3 መኝታ መኖሪያ በስጦታነት በሚያስገኝ የ 1.5 ሚሊዮን ብር ዋጋ ማቅረቡ ይታወሳል።

በመጀመሪው የማስታወቂያ ሽያጭ በ15 ቀናት ውስጥ 1 ቢሊዮን ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በስኬት በተጠናቀቀው የታወር ባለአክሲዮን ሥርዓት አክሲዮን ሽያጭ ላይ 1 ሺህ ሰዎች አክሲዮኖችን በመግዛት የኩባንያው ባለቤት ከመሆናቸው ባለፈ የባለ ሦስት መኝታ መኖሪያ ቤት በስጦታ የሚያገኙበትን ወርቃማ ዕድል ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

ምስል በነብዩ ዳንኤል



"

**በስብሰባው ላይ የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ስለ አጠቃላይ የመሬት ግዢ ሒደቱ እና የአክሲዮን ሽያጩን በተመለከተ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን በተለያዩ የመንግሥት እና የማኅበራዊ ትስስር ገጾች በተሰራጩ መሠረት አልባ ውንጀላዎች ምክንያት የገጠሙንን የገጽታ ግንባታ እንቅፋቶች እንዲሁም ለግንባታ በተፈቀደው መሬት ላይ ፍላጎት ባላቸው ባለሃብቶች እና ስልጣንን አለአግባብ በሚጠቀሙ የመንግሥት አካላት የተከፈተብንን ኢ-ፍትሐዊ አካሄድ ለመከላከል ባለአክሲዮኖች በጋራ እንዲቆሙ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።**

ኩባንያው በ15 ቀናት ውስጥ ለመሰብሰብ ያቀደውን 1 ቢሊዮን ብር ከተቀመጠለት የጊዜ ገደብ አስቀድሞ በመሰብሰብ ፕሮጀክቱ ለሚገነባበት ቦታ ግዢ ቅድመ ክፍያ ለመፈጸም ዝግጅቱን ቢያጠናቅቅም ገንዘቡ መሬቱን ወደ ሸጠው አካል እንዳይተላለፍ በማገድ ክፍያው ተጠናቆ ቦታውን መረከብ እንዳይችል የሚያደርጉ ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች ገጥመውታል።

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ማብራሪያ በቴሌቪዥን ጣቢያዎችና በማኅበራዊ የትስስር ገጾች የሚሰራጩ መረጃዎች እንዲሁም በመንግሥት ተቋማት የወጡ ማስጠንቀቂያዎች የድርጅቱን መልካም ስም በማጠልሸትና የቆመለትን ታላቅ ዓላማ ጥያቄ ውስጥ በማስገባት አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደራቸው የተጠቆመ ሲሆን ከዚህም ባለፈ 20 ሺህ ባለአክሲዮኖች ያሉትን ይህን ግዙፍ ተቋም የባንክ ሒሳቦች እንዲታገዱ በማድረግ የዕለት ተዕለት ሥራዎች እንዲስተጓጎሉ አድርጓል ተብሏል።

ምስል በነብዩ ዳንኤል



**ይህንንም ኩባንያው በሕጋዊ መንገድ ለሚመለከተው የመንግሥት ቢሮ ከማስታወቁም በተጨማሪ ባንኮችን፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን እና የተለያዩ ማኅበራትን ጨምሮ 17 አባል ድርጅቶችን ያካተተ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ የከገበሬውን ሕንጻ የሚያካትተውን ታወር ሼር ሆልደር ሞዴል ፕሮጀክት የመቆጣጠርና የመከታተል ሚና እንዲኖረው ጥሪ መቅረቡን ዋና ሥራ አስፈጻሚው አስታውሰዋል።**

በየትኛውም ድርጅት ባልተለመደ መልኩ አንድ የግል ኩባንያ የውስጥ አሠራሩን መንግሥት እንዲፈትሽ መፍቀዱ ተቋማዊ ተአማኒነቱን የሚያረጋግጥ መሆኑን የገለጹት ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ታወር ሼር ሆልደር ሞዴል ፕሮጀክት በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረውን ትልቅ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉም አካላት ከፐርፐዝብላክ ጎን እንዲቆሙ ጥሪ አቅርበዋል።

የጋዜጠኝነት ሙያን ሕግ የጣሱና ሚዛናዊነቱን በጠበቀ መንገድ እውነታን መሠረት ያደረገ መረጃ ከማቅረብ ይልቅ በተዛባ መልኩ የኩባንያውን ስም የሚያጎድፉ መረጃዎች በማኅበራዊ የትስስር ገፆች ሲንሸራሸሩ መቆየታቸው በጉባኤው የተጠቆመ ሲሆን በተጨማሪም በመንግሥት ተቋም ፐርፐዝብላክን በተመለከተ የማጭበርበር ድርጊት በሚል የወጣውን መረጃ ተከትሎ ኩባንያው መከሰሱ ተጠቁሟል።

ኩባንያው የተነሡበት የክስ ነጥቦች የተሰበሰበውን ገንዘብ የሰበሰበው አካል ወይም ሰዎች ይዘውት ቢጠፉስ፣ በማጭበርበር ካልሆነ በዚህ ፍጥነት እንዴት ይህን ያህል ገንዘብ ይሰበሰባል፣ አጓጊ እና የማይታመን ቃል ገብታችኋል፣ ከተጠቀሰው አላማ በተጨማሪ ድብቅ አጀንዳ ቢኖረውስ እና መሬት ሳይኖራችሁ አለን ብላችኋል የሚሉ መሆናቸውም በጉባኤው ተነስቷል።



ምስል በነብዩ ዳንኤል

> “
>
> **በውይይቱ ተሳታፊ ከሆኑ ባለአክሲዮኖችም ጥያቄና አስተያየቶች የተሰነዘሩ ሲሆን ኩባንያው በታወር ሼር ሆልደር ሞዴል አክሲዮን ካቀረበው የኩባንያው ባለቤትነት ዕድል እና የባለ 3 መኝታ መኖሪያ ቤት ስጦታ በተጨማሪ በራዕዩ አምነው የTCTዝብላክ ቤተሰብ መሆናቸውን ገልጸው የስም ማጥፋት ዘመቻውንም ሆነ በተለያዩ አካላት እየተደረጉ ያሉ ጫናዎችን ለመቃወም በጋራ እንቆማለን ብለዋል።**

በመጨረሻም የታወር ሼር ሆልደር ሞዴል ባለአክሲዮኖች በኩባንያው ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም ለመውሰድና አስፈላጊውን ሕጋዊ እንቅስቃሴ ለማከናወን በበጎ ፈቃደኛ ባለአክሲዮኖች ሁሉንም የታወር ሼር ሆልደር ሞዴል ባለአክሲዮኖች በመወከል ኩባንያው የገጠመውን ወቅታዊ ሁኔታ ጨምሮ የሕንጻ ግንባታውን በተመለከተ ከፐርፐዝላክ ኢትዮጵያ ቦርድ እና ከፍተኛ አመራሮች ጋር በቅርበት የሚሠራ 11 አባላት ያሉት ግብረኃይል ተቋቁሟል።

## TCTዝብላክ ኢትዮጵያ በአገራችን ቀዳሚ የኢኮሜርስ ገበያ አማራጭ ሊያደርጉት የሚያስችሉትን ሦስት ፕሮጀክቶች በይፋ ሊያስጀምር መሆኑ ተገለጸ።

የከገበሬው ኢ-ኮሜርስ ክፍል ለወራት በትኩረት ሲሠራበት የቆየውን ከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንት፣ ብሔራዊ የምርት ስርጭት አገልግሎት እና የከገበሬው የጥሪ ማእከልን በይፋ ሊያስጀምር መሆኑን የከገበሬው ኢ-ኮሜርስ ኃላፊ አቶ አማኑኤል መለሰ አስታውቀዋል።

ኃላፊው በመጪው ቅዳሜ ሰኔ 24 2015 ዓ.ም እነዚህን ግዙፍ ፕሮጀክቶች የኩባንያው ባለአክሲዮኖች፣ ታማኝ ደንበኞች፣ በሥራ ፈጠራ እና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ላይ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች እንዲሁም በተለያየ የሙያ ዘርፎች የተሰማሩ እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በይፋ እንደሚያስጀምር የገለጹ ሲሆን ሦስቱም ፕሮጀክቶች የፐርፐዝብላክ ደንበኞችን ጨምሮ በመላው አገሪቱ የሚኖሩ ዜጎች ርቀት ሳይገድባቸው ያሻቸውን እንዲገበያዩ ከማስቻላቸው በላይ በወኪልነት በመሥራት ገቢ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል ብለዋል።

KEGEBEREW E-COMMERCE

> “
>
> **ከግብርና ምርቶች እና የማቀነባበሪያ ውጤቶች በተጨማሪ ምርትና አገልግሎት አቅራቢዎች፣ አምራቾች እና ገዢዎች በአንድ ቦታ የሚገናኙበት የበይነ መረብ ሥርዓት በሆነው ከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንት ሲስተም ከቤት እቃና መድኃኒቶች ጀምሮ እስከ ጸረ-አረም እና ማሽነሪዎች በመላ አገሪቱ የሚያዳርስ የግብይት መድረክ መሆኑን በመግለጽ በአዲስ አበባ እና በዋና ዋና የክልል ከተሞች ተግባራዊ እንደሚደረግ የተናገሩት ኃላፊው ሴቶች እና ወጣቶችን ቀዳሚ ባደረገው የወኪል አከፋፋይነት ሥራ ሁሉም ተጠቃሚ እንዲሆን ግብዣ አቅርበዋል።**

በመላው አገሪቱ የሚመረቱ የተለያዩ የግብርና፣ አግሮ ኢንዱስትሪ እና የፋብሪካ ምርቶችን ስርጭት የሚያስተባብር እና የሚቆጣጠር የሎጂስቲክ ቡድን እየተቋቋመ እንደሆነ በማስታወስ ገዢዎችን ወደ ኩባንያው ለሚያመጡ ወኪሎችና ምርቶችን ለሚሸጡ ድርጅትና ግለሰቦች ሥራው በተጠናቀቀበት ፍጥነት ክፍያ ለመፈጸም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን አስረድተዋል።

የከገበሬውን ጥሪ ማእከል በተመለከተ ለማእከሉ ግንባታ አስፈላጊ የዝርጋታና የእቃ ግዢ ሥራዎች መከናወናቸውን ይፋ ያደረጉት ኃላፊው ከ20 ያላነሱ ሠራተኞችን በመቅጠር በመጪው ሳምንት በይፋ ሥራውን ይጀምራል ብለዋል።

ይህም የከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንትን እና የብሔራዊ ምርት ስርጭትን ጨምሮ በመላ አገሪቱ ከሚገኙ አምራችና ሸማቾች እንዲሁም የኩባንያው ባለአክሲዮኖች በ9858 የሚደረጉ ጥሪዎችን በማስተናገድ ከፐርፐዝብላክ ጋር ትስስርን በመፍጠር እንቅስቃሴውን ይበልጥ ቀልጣፋ ከማድረግ አንጻር ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋልም ብለዋል።

በመጨረሻም እነዚህ ሦስት ፕሮጀክቶች አስፈላጊው ድጋፍ እና ክትትል ተደርጎላቸው ውጤታማነታቸው እውን ይሆናል ያሉት አቶ አማኑኤል በኩባንያው ማእቀፍ ስር የሚንቀሳቀሱ ራሳቸውን የቻሉ ድርጅቶች እስኪሆኑ ድረስ በትኩረት እንደሚሠራባቸውም አስታውቀዋል።

**የከገበሬው አግሮ ፕሮሰሲንግ ክፍል ጥራቱን የጠበቀ የእንጀራ ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ ሊያቀርብ መሆኑን አበሠረ።**

የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አግሮ ፕሮሰሲንግ ክፍል በአዲስ አበባ ዓድዋ ድልድይ አካባቢ በሚገኘው የዳቦ ማምረቻ ከሚያመርታቸው የዳቦ እና ተያያዥ ምርቶች በተጨማሪ የእንጀራ ማቀነባበሪያ ለማቋቋም ማቀዱን የክፍሉ ኃላፊ አቶ ሽመልስ ጥላሁን ገለጹ።

ኃላፊው ለግንባታው አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶች እየተደረጉ መሆናቸውን በመጠቆም የእንጀራ ማምረቻው በርካታ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር በከተማው የናረውን የእንጀራ ዋጋ ከማረጋጋት ባሻገር ምርቶቹን የሸማቹን የመግዛት አቅም ባገናዘበ ዋጋ ተደራሽ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ተናግረዋል።



Abobe Stock

> **በምርት ሒደቱ ላይ የምግብን ደኅንነት ከማስጠበቅ አንጻር ኩባንያው ከዚህ ቀደም ተግባራዊ ሲያደርግ እንደቆየው አስፈላጊ የሆነ የአቅም ግንባታ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የተለያዩ ስልጠናዎችን ለሠራተኞች ለመስጠት መዘጋጀቱን ያነሡት ኀላፊው በዚህ ሒደት ከኩባንያው የጥራት ክፍል ጋር ከመቼውም በበለጠ በቅርበት መሥራት እንደሚጠበቅበት ገልጸው የግል እና የመገልገያ መሣሪያዎችን ንጽሕና፣ የሥራ ቦታ ደኅንነት እና አለባበስ እንዲሁም ተያያዥ ርእሰ ጉዳዮች ትኩረት እንደሚሰጣቸው ጠቁመዋል።**

አቶ ሽመልስ አክለውም በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆኑ የተለያዩ የከገበሬው ማቀነባበሪያ ምርቶችን በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች በማምረት ተደራሽ ለማድረግ የሚሠራው የከገበሬው አግሮ ፕሮሰሲንግ ክፍል የተለያዩ የባልትና፣ የዳቦ እንዲሁም ተለቅመው የሚታሸጉ የእህል እና ጥራጥሬ ምርቶችን በከፍተኛ ጥራት በማዘጋጀት ለገበያ እያቀረበ እንደሚገኝ ያስታወቁ ሲሆን በከገበሬው የዳቦ መጋገሪያና መሸጫ የተለያየ ዓይነት ይዘትና ጣዕም ያላቸውን ዳቦና ተያያዥ ምርቶችን በማምረት ዓድዋ ድልድይ፣ ሰሚት፣ አትላስ፣ ቡልቡላ፣ አያት እና ላፍቶ በሚገኙት የከገበሬው ሱቆች እንዲሁም ለቋሚ ደንበኞቹ ያሰራጫልም ብለዋል።

የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አግሮ ፕሮሰሲንግ ክፍል በምርት ሒደቱ እንደ ዱቄት፣ እርሾ፣ የዳቦ ማሻሻያ፣ ዘቢብ፣ ቴምር የመሳሰሉትን ለዳቦ ምርት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እና የዳቦ መጋገሪያ መሣሪያዎችን በተፈለገው ጊዜ እና መጠን በማቅረብ ጥራታቸውን የጠበቁ የማቀነባበሪያ ውጤቶችን ለገበያ ማድረስ መቻሉ ተጠቁሟል። በቀጣይም የዳቦ ምርት ዓይነቶችን በማብዛት እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማኅበረሰቡ በማቅረብ የኩባንያውን የኑሮ ውድነትን ታሪክ የማድረግ ራዕይ ለማሳካት የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት ተገልጿል፡፡





ምስል በኤደን ደነቀ

> **በተመሳሳይ ክፍሉ መካኒሳ አካባቢ በሚገኘው የምርት ማዘጋጃ ተለቅመው፣ ተበጥረው እና ታጥበው ለአያያዝ ምቹ በሆነ አስተሻሸግ ለገበያ ከሚያቀርባቸው እህልና ጥራጥሬዎች በተጨማሪ በአርባ ምንጭ ከተማ ባደራጀው የባልትና ምርቶች ማቀነባበሪያ ለምግብ ማብሰያነት የሚውሉ በርበሬ፣ ሽሮ፣ የተፈጩ እህሎች እና የተለያዩ ቅመማ ቅመሞችን በጥራት እያመረተ እንደሚገኝም አቶ ሽመልስ ተናግረዋል።**

በቀጣይም ግብአቶች በተሻለ መጠን እና ጥራት እንዲቀርቡ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በቅርበት በመነጋገር በተለይም ከምርት አቅርቦት ክፍል እና ከከገበሬው ሱቆች ጋር የተቀናጀ እንቅስቃሴ እያከናወኑ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

በስድስቱ የከገበሬው ሱቆች ብቻ የተወሰነውን የአቅርቦት አቅምም በማሳደግ ይበልጥ ሰፊ በሆነና በተደራጀ መልኩ ለተለያዩ ሱቆች፣ ምግብ ቤቶች እንዲሁም የንግድ ተቋማት በማሰራጨት ምርትና ትርፋማነትንም ለመጨመር በዝግጅት ላይ የሚገኘው የአግሮፕሮሰሲንግ ክፍል አዳዲስ የመጋገርያ ቅርንጫፎች እና ሱቆች ለመክፈት በዝግጅት ላይ እንደሚገኝም ኃላፊው አውስተዋል።

በመጨረሻም አቶ ሽመልስ የሙብራት እና ውሀ ኃይል አቅርቦት ማነስ እና መቆራረጥ እንዲሁም የማምረቻ ቦታ ጥበት ክፍሉ የገጠሙት ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው ያሉ ሲሆን እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በቅርበት ከመሥራት አንስቶ በበላይ አመራር ትኩረት የሚሹ የማሽነሪ ግዢዎች እና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን የማስተባበር ጉዳዮች ላይ በርካታ የለውጥ ጥረቶች እየተደረጉ እንደሆነ ገልጸዋል። ሥራዎችን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግም ከተለያዩ የኩባንያው ክፍሎች ጋር በመቀባበል እየሠራን ነው ያሉት ኃላፊው ሰፊ የገበያ መዳረሻዎችን በማመቻቸት በበቂ ሁኔታ ምርት ማቅረብ እንዲቻል ዘርፈ ብዙ ሥራዎች መጀመራቸውንም ጠቁመዋል።

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከባሰሚን ፖሊተሪ ፋርም ጋር በፍራንቻይዝ በሚያከናውነው የዶሮ እርባታ አበረታች ውጤት መታየቱ ተገለጸ።

ከሁለት ወራት በፊት ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከባስሚን ሞደርን ፖሊተሪ ፋርም ጋር በመቀናጀት የወጠነው የመጀመሪያ ዙር የዶሮ እርባታ ሒደት በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ እንስሳት እርባታ ክፍል አስተባባሪ አቶ ታጋይ መንግሥቱ አስረድተዋል።

ኩባንያው በሆለታ ከተማ አዲስ ዓለም አካባቢ 20 ሺህ ዶሮዎችን የመያዝ አቅም ያላቸው 9 ዘመናዊ የዶሮ ቤቶችን በማደራጀት ለእርባታው ማስጀመሪያ 2000 የአንድ ቀን ጫጩቶችን እያረባ የሚገኝ ሲሆን እንደየጊዜያቸውና የእድገት ደረጃቸው የተመጣጠነ ምግብና ንጹሕ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲሁም አስፈላጊው ህክምና እየተደረገላቸው እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ምስል በኑብዩ ዳንኤል



> እያንዳንዱ መጠለያ 1 ሺህ ዶሮዎችን የመያዝ አቅም እንዳለው የገለጹት አቶ ታጋይ በጥቂት ቀናት ውስጥ ተጨማሪ 2000 ጫጩቶችን ለማስገባት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም ተናግረዋል።

ዶሮዎቹ በ 45 ቀናት ውስጥ ለስጋ እንደሚደርሱና ከእርድ ጋር በተያያዘ ለሚያስፈልገው ከፍተኛ ንጽሕና የፐርፐዝብላክ ግብርና ክፍል አርደው፣ አጥበውና በልተው ደረጃውን በጠበቀ አስተሻሸግ ለከገበሬው ሱቆች የሚያቀርቡ ድርጅቶችን የማነጋገር ሒደቱም እየተከናወነ እንደሚገኝ ተጠቁሟል።

ሆለታ በሚገኘው በዚሁ የዶሮ እርባታ 1 ፋርም ማናጀር እና 14 ሠራተኞች መቀጠራቸውን ያስታወሱት ኃላፊው በቀጣይ በሚጀመሩት ከእንስሳት እርባታ ጋር በተያያዙ እንቅስቃሴዎችም ለበርካቶች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደሚቻልም አመላክተዋል። የግብርና ክፍሉ ለ2016 ዓ.ም የዘመን መለወጫ በርካታ ዶሮዎችን ለገበያ ለማቅረብ ማቀዱን በመጠቆም በቅርቡ 6 ሺህ የአንድ ቀን ጫጩቶችን እንደሚያስገባ አቶ ታጋይ አስታውቀዋል።

በተያያዘ ዜናም ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በአርባምንጭ ከተማ ዳጎሞቴ እርሻ የእንስሳት እርባታ እና የመኖ ልማት ለመጀመር ከጥቂት ቀናት በፊት ፈቃድ ማግኘቱን እና መሬት መረከቡን ተከትሎ ዓመታዊ ዕቅድ ተነድፎ ወደ ተግባር መግባቱን ይፋ አድርገዋል። አስተባባሪው "ለመጀመሪያ ዙር 100 የሚደልቡ ከብቶችና 200 ፍየሎችን ለማስገባት የሚያስችለው የመጠለያ ግንባታ መጀመሩን ገልጸው በተመሳሳይ በዳጎሞቴ በሚከናወነው የእርሻ ሥራም ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ሃባብ፣ ቃሪያ፣ ፓፓያ፣ ዝኩኒ እና ሌሎች አትክልትና ፍራፍሬዎችን በማምረት ሒደት ላይ እንደሚገኝ ጠቁመው ምርቶቹም በቀጥታ በ6ቱም የከገበሬው ሱቆች ተሰራጭተው በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቾች እየደረሱ እንደሚገኙም ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የግብርና ክፍሉ በደቡብ ምእራብ ክልል ከፋ ዞን ጠሎ ወረዳ ሻናቶ ቀበሌ በክላስተር ባደራጃቸው አርሶ አደሮች አማካኝነት ለማልማት በዕቅድ የያዘውን ቦታ የመስክ ጉብኝት ያካሄደ ሲሆን አርሶአደሮቹ የፐርፐዝብላክ ባለቤት መሆን የሚያስችላቸውን አክሲዮን መግዛታቸውን እንዲሁም እርሻዎቻቸውን ከኩባንያው ጋር በጥምረት ለማልማት ውል መግባታቸውን የከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር ሥራ አስኪያጅ አቶ አብርሃም ተፈረደኝ አስታውቀዋል።

ምስል በኑብዩ ዳንኤል



> ዋና ሥራ አስኪያጁ እንደገለጹት በክልሉ ለፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው በሆነው በዚህ ክላስተር አርሶ አደሮቹ ከዚህ ቀደም ተደራጅተው ሲሠሩ የነበሩና በዚሁ መሬት የዘር ብዜት ሲያከናውኑ የቆዩ መሆናቸውን እና ገበሬዎቹ ከኩባንያው ጋር በጋራ ለማልማት ባገኙት ዕድል መደሰታቸውን እና በዘመናዊ መንገድ በማልማት ምርታማነታቸውን ከመጨመር አንጻር በፐርፐዝብላክ ባለሙሉ ተስፋ መሆናቸውን እንዳረጋገጡ አብራርተዋል።

ከመሬቱ አስቸጋሪ አቀማመጥ የተነሣ የእርሻ መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎችን ወደቦታው ለማድረስ አዳጋች መሆኑን ያስታወሱት አቶ አብርሃም በደቡብ ምእራብ ከፍተኛ ስፍራ በሚገኘው በዚህ እርሻ ጉብስን እና ድንችን ጨምሮ ሌሎችንም የደጋ ሰብሎች ለማልማት መታቀዱን አስታውቀዋል። ወቅቱ የዝግጅት በመሆኑም የእርሻ ሥራ መጀመሩን እና በመጪው የነሐሴ ወርም ወቅቱን የጠበቀ ዘር እንደሚዘራ ተናግረዋል።

ዋና አዘጋጅ፡ ሰላማዊት ደበበ
ሲንየር ሪፖርተር፡ ጌታባለው ገ/ሐና
ሪፖርተር፡ ኤደን ደነቀ

ለበለጠ መረጃ
ስንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ
+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222
7151
www.purposeblackethiopia.com